የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፻፮
አዲስ አበባ ጳጉሜ ፫ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No. 106
ADDIS ABABA 8th September , 2016

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፯/፪ሺ፰ ዓ.ም

ለአራተኛው የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ.........ገጽ ፱ሺ፫፻፰

**CONTENT**

Proclamation No. 977/2016

International Development Association Additional Financing Agreement for productive safety net Project IV Ratification Proclamation..................................Page 9308

## አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፯/፪ሺ፰

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

ለአራተኛው የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ፸ ሚሊዮን ፮፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሰባ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) የሚያስገኘው የተጨማሪ ብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፳፬ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የተጨማሪ ብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፴ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡-

## PROCLAMATION NO. 977/2016

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION**

**WHEREAS**, Additional Financing Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association Provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit in an amount not exceeding 70,600,000 SDR (seventy million and six hundred thousand SDR) Special Drawing Rights for additional financing productive safety net Project IV was signed in Addis Ababa on the 1st day of July, 2016.

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Additional Financing Agreement at its session held on the 7th day of July, 2016;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

፩. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ አዋጅ "ለአራተኛው የልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፯/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. የ<u>**ስምምነቱ መጽደቅ**</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል ሰኔ ፳፬ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የተጨማሪ ብድር ስምምነት ቁጥር 5877-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

፫. <u>**የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን**</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በተጨማሪ የብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፸ ሚሊዮን ፮፻ ሺ ኤስ.ዲ.አር (ሰባ ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር) በተጨማሪ ብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬. <u>**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ጳጉሜ ፫ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. <u>**Short Title**</u>

This Proclamation maybe cited as the "International Development Association Additional Financing Agreement for productive safety net Project IV Ratification Proclamation No. 977/2016."

2. <u>**Ratification of the Agreement**</u>

The Additional Financing Agreement Number 5877-ET signed in Addis Ababa on the 1st day of July, 2016, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and International Development Association is hereby ratified.

3. <u>**Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation**</u>

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of 70,600,000 SDR (seventy million and six hundred SDR) Special Drawing Rights in accordance with the trems and conditions set forth in Additional Financing Agreement.

4. <u>**Effective Date**</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 8th day of September, 2016.**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**